# የሴት ልጅ ግርዛት (ባህላዊ መቆረጥ) እና የአውስትራሊያ ህግ

## የሴት ግርዛት ወይም 'ባህላዊ የሴት መቁረጥ' በአውስትራሊያ ውስጥ ከህጉ ጋር ይቃረናሉ።

### የሴት ልጅ ግርዛት ምንድን ነው?

የሴት መገረዝ ወይም የሴት ብልት መቁረጥ Female Genital Cutting (FGC) ተብሎም የሚጠራው ባህላዊና ልምዳዊ ተግባር ነዉ። የውጪውን የሴት ብልት አካባቢ፣ ከንፈርና እና ቂንጥር መቁረጥን ያካትታል። ምንም ዓይነት የጤና ጠቀሜታ የሌለው ከመሆኑም በላይ የአንድን ሰው የጾታና የወሊድ ጤንነት ሊጎዳ ይችላል።

### ይህንን ልምድና ተግባር በተመለከተ ህጉ ]]ምን ይላል?

በማንም የሴት ልጅ ግርዛት መፈጸም ህጉን ይቃወማል።

በጤና ምክንያት በሀኪም ካልተደረገ በስተቀር የሚከተሉት ተግባራት ህገ ወጥ ናቸው፡

- ቂንጥርንና የብልት ከንፈርን ጨምሮ ማንኛውንም የሴት የብልት ክልል (excision) ማስወገድ ወይም መቁረጥ
- የብልት አካባቢን አንድ ላይ ማጣበቅ ወይም መስፋት (infibulation)
- ማናቸውም የብልት ክፈተትን ለማጥበብ ወይም ለመዝጋት የሚደረግ ቀዶ ጥገና
- ኪንጥርን ወይም የቂንጥርን ክፍል መቁረጥ (clitoridectomy)
- የጾታ ብልት አካባቢን መጉዳት ወይም መቁረጥ።

በቪክቶሪያም እነዚህን ማድረግ ህገ-ወጥነት ይሆናል፡

- ለሴት ግርዛት አንድን ሰው በየትኛውም በአውስትራሊያ ውስጥ ወይም ወደ ወደ ሌላ አገር መውሰድ
- የሴት ልጅ ግርዛትን እንዲያካሂዱ አንድን ሰው መርዳት
- የሴት ግርዛትን የሚፈጽም ሰው መፈለግ።

**አንድ ሰው በቀዶ ጥገና ሂደቱ ቢስማማም፣ ወይም ወላጆቹ ቢፈቅዱለት እንኳ አሁንም ቢሆን ህገ-ወጥ ነው።**

### አንድ ሰው ህጉን ቢጥስ ምን ይሆናል?

አንድ ሰው ህግ የሚጥሰው እነዚህን ሲያደርግ ነዉ፡

- ቀዶ ጥገናዉን ወይም ተግባሩን መፈጸም
- አንድ ሰው ይህን ለማካሄድ መርዳት
- ይህን የሚሰራ ሌላ ሰው ፈልጎ ማገናኘት።

በቪክቶሪያ ውስጥ፣ ቅጣቱ እስከ 15 ዓመት የሚደርስ እስራት ሊሆን ይችላል።

### የሆነ የቀዶ ጥገና ህክምና ማድረግ ይፈቀዳልን?

በአንዳንድ ሁኔታዎች በሴቶች የጾታ ብልት ላይ የቀዶ ጥገና ህክምና ማድረግ ይፈቀዳል። አንድ የህክምና ባለሙያ ወይም አዋላጅ ነርስ እነዚህን አሰራሮች መቼ ሊያከናውን እንደሚችል፡

- ለጤና ምክንያት የቀዶ ጥገናው የሚያስፈለግ ከሆነ
- በምጥ ላይ ወይም ወዲያውኑ ከወሊድ በኋላ አስፈላጊ ከሆነ።

በተጨማሪም አንድ የህክምና ዶክተር ጾታን የሚያረጋግጥ ቀዶ ጥገና ህክምና ከሆነ በሴት ብልት ላይ ቀዶ ህክምና ማድረግ ይችላል።

### አንድ ሴት ልጅ ከወለደች በኋላ እንደገና መሰፋት (re-infibulated) ወይም ሌላ ዓይነት የማህጸን የቀዶ ጥገና ህክምና ሊደረግላት ይቻላልን?

በፍጹም፤ የሴት ብልትን ለማጥበብ ወይም ለመዝጋት ዳግም-መዝጋት infibulation ማድረግ ያለ ጤና ምክንያት አይፈቀድም።

ይሁን እንጂ፣ ከወሊድ በኋላ የተቀደደ ወይም ቀዶ ጥገና ህክምና ከተደረገ መስፋት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ይህ የሚደረገው በአንድ የህክምና ዶክተር ወይም አዋላጅ ነርስ ከወሊድ ብዙም ሳይቆይ ነው።

## በአንዲት ልጅ የሴት ግርዛት (ባህላዊ ቆረጣ) ለባለስልጣናት ሪፖርት የሚያደርገው ማን ነው?

በቪክቶሪያ ውስጥ የሴቶች ግርዘት ህገ-ወጥ ሲሆን ከ18 ዓመት በታች በሆነ ልጅ ላይ ከተፈጸመ በልጆች ላይ የሚፈጸም ጥቃት/በደል እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል።

ይህም ማለት እንደ ዶክተሮች፣ ነርሶች፣ አዋላጅ ነርሶች፣ መምህራን፣ የህጻናት እንክብካቤ መስጫ ሰራተኞች እና ፖሊስ የመሳሰሉ ከህጻናት ጋር የሚሰሩ ሰዎች አንድ ልጅ ተገረዘች ብለው የሚጠራጠሩ ከሆነ ለጤናና ለሰብአዊ አገልግሎት መስሪያ ቤት ማሳወቅ አለባቸው ማለት ነው።

ይሁን እንጂ ማንኛውም ሰው ለጤናና ለሰብዓዊ አገልግሎት መሥሪያ ቤት (Department of Health and Human Services) ሪፖርት ማቅረብ ይችላል።

## ለበለጠ መረጃ

የቤተሰብና የወሊድ መብት ትምህርት ፕሮግራም (Family and Reproductive Rights Education Program - FARREP) ሰራተኞች ከሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 9am እስከ ምሽቱ 5pm ሰዓት ድረስ ይገኛሉ።

ተለፎን፡ (03) 8345 3058
ኢሜል: farrep.program@thewomens.org.au
ፋክስ፡ (03) 8345 3053

ወይም በአካባቢዎ ማህበረሰብ ጤና ማእከል ውስጥ የFARREP ሰራተኛን ያነጋግሩ።

ለበለጠ መረጃ በድረገጻችን ገብተው ይፈልጉ፡
http://www.thewomens.org.au/health-information

## የቋንቋ አገናኝ መርበብ

**በርስዎ ቋንቋ መረጃ ለማግኘት በድረገጻችን ላይ ይጎብኙ**
للحصول على المعلومات بلغتك زوروا موقعنا الإلكتروني
用您說的語言瞭解詳情，請瀏覽我們的網站
Για πληροφορίες στη γλώσσα σας επισκεφθείτε την ιστοσελίδα μας
अपनी भाषा में जानकारी प्राप्त करने के लिए हमारी वेबसाइट पर जाइए
Per informazioni nella vostra lingua visitate il nostro sito web
Macluumaad intaas ka badan oo af Somali ah booqo websaytkayaga
Kendi dilinizde bilgi almak için web sitemizi ziyaret edin
Để biết thông tin bằng ngôn ngữ của quý vị, hãy truy cập trang mạng của chúng tôi

## አስተርጓሚ ይፈልጋሉን?

Interpreter

የሚያስፈልግዎ ከሆነ አስተርጓሚ መጠየቅ ይችላሉ።

## የቤተሰብ ጥቃት ድጋፍ

**1800 Respect National Helpline/እርዳታ መስመር**

ወሲባዊ ጥቃት፣ በቤት ውስጥ ወይም በቤተሰብ ውስጥ ጥቃት ከደረሰብዎት እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።
በቀንም ሆነ በሌሊት በማንኛውም ሰዓት መደወል ይችላሉ።
በስልክ 1800 737 732 (24-ሰዓት የድጋፍ አገልግሎት)
1800respect.org.au

## የህግ ማጣቀሻዎች

### የቪክቶሪያ ህጎች

- የወንጀል ኣንቀጽ ህግ (Crimes Act) 1958 (Vic) s32 – 34A
- ህጻናት፤ ወጣት እና የቤተሰብ ኣንቀጽ ህግ (Children, Youth and Families Act) 2005 (Vic) s162, s163, s182, s184

### ሌላ የኣውስትራሊያ መስተዳድር ግዛትና ተሪቶርይ ህጎች

- የወንጀል ኣንቀጽ ህግ (Crimes Act) 1900 (ACT) s73-s77
- የወንጀል ኣንቀጽ ህግ (Crimes Act) 1900 (NSW) s. 45,s45A
- የወንጀል ኮድ ኣንቀጽ ህግ (Criminal Code Act) (NT) Division 4A
- የወንጀል ኮድ ኣንቀጽ ህግ (Criminal Code Act) 1899 (Qld) 323A, 323B
- የወንጀል ህግ ማጠናከሪያ ኣንቀጽ ህግ (Criminal Law Consolidation Act) 1935 (SA) ክፍል/Division 8
- የወንጀል ኮድ ኣንቀጽ ህግ (Criminal Code Act) 1924 (Tas) s178A
- የወንጀል ህግ ኮድ ማቀናበሪያ ኣንቀጽ ህግ (Criminal Code Act Compilation Act) 1913 (WA) s306

**የክህደት ቃል፡** ይህ የመረጃ ወረቀት አጠቃላይ መረጃን ብቻ ያቀርባል። ስለ ጤና አጠባበቅ የሚያስፈልግዎን ነገሮች በተመለከተ ግልጽ የሆነ ምክር ለማግኘት ከጤና ባለሞያዎ ምክር መጠየቅ ይኖርብዎታል። የሮያል የሴቶች ሆስፒታል (The Royal Women's Hospital) የጤና ባለሙያን ከማየት ይልቅ በዚህ የመረጃ ወረቀት ላይ በመተማመን ለሚደርስ ጉዳት ወይም ኪሳራ ምንም አይነት ሀላፊነት አይወስድም። አጣዳፊ የህክምና እርዳታ የሚያስፈልግዎት ከሆነ እባክዎ በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው የድንገተኛ አደጋ ክፍል ሂደዉ ያነጋግሩ። © The Royal Women's Hospital 2025